# የስቶክሆልም ኤምባሲ
# የአገልግሎት ቻርተር

(የተሻሻለ)

ጥር 2010 ዓ.ም.

ስቶክሆልም

<u>ማ ው ጫ</u>


| ተ.ቁ | ርዕስ | ገጽ |
|---|---|---|
| 1. | የተቋሙ ስም | 3 |
| 2. | የሚሲዮኑ ተልዕኮ | 3 |
| 3. | የቻርተሩ ዓላማ | 3 |
| 4. | የሚሲዮኑ ዕሴቶች እና መገለጫዎች | 3 |
| 5. | የምንከተላቸው መርሆዎች | 5 |
| 6. | የኤምባሲው ተገልጋዮች | 5 |
| 7. | የተገልጋዮች መብት | 6 |
| 8. | የተገልጋዮች ግዴታ | 6 |
| 9. | ከሚሲዮኑ የሚጠበቁ ውጤቶች | 6 |
| 10. | ለተገልጋዮች የምንገባው ቃል | 6 |
| 11. | ተሳትፎና ግብዓት | 6 |
| 12. | የቅሬታ አቀራረብ ስርዓት | 7 |
| 13. | የመረጃ ማስተላለፊያ መንገዶች | 8 |
| 14. | የክትትልና ግምገማ ሥርዓት | 9 |
| 15. | በኢኮኖሚና ቢዝነስ ማስፋፊያ ዘርፍ የሚሰጡ አገልግሎቶች | 10 |
| 16. | በቆንስላ ጉዳዮች ዘርፍ የሚሰጡ አገልግሎቶች | 12 |
| 17. | በዳያስፖራ ዘርፍ የሚሰጡ አገልግሎቶች | 21 |
| 18. | በፐብሊክ ዲፕሎማሲ ዘርፍ የሚሰጡ አገልግሎቶች | 25 |

# <u>የኢ.ፌ.ዲ.ሪ. ኤምባሲ ስቶክሆልም</u>

# <u>የአገልግሎት ቻርተር</u>

**1. የተቋሙ ስም ፡ የኢፌዲሪ ኤምባሲ ስቶክሆልም**

**2. የሚሲዮኑ ተልዕኮ**

ከኖርዲክ አገሮች ጋር ያለንን የዲፕሎማሲ ግንኙነት ወደ ላቀ ደረጃ በማሸጋገር፣ መልካም ገጽታችንን በመገንባት፣ የዲያስፖራ ተሳትፎን በማጠናከር፣ የውጭ ቀጥታ ኢንቨስትመንትና የልማት ፋይናንስ እንዲሁም ንግድና ቱሪዝም በማሳደግ አገራዊ ጥቅምን በማስጠበቅ ለሀገራችን ሰላም፣ ልማትና ዴሞክራሲያዊ ስርአት ግንባታ የጎላ አስተዋጽኦ ማበርከት ነው፡፡

**3. የቻርተሩ ዓላማ**

ኤምባሲው በሚሸፍናቸው በስዊድን፣ ዴንማርክ፣ ፊንላንድ፣ ኖርዌይ እና አይስላንድ አገሮች ለሚኖሩ ኢትዮጵያዊያንና ትውልድ ኢትዮጵያዊያን እንዲሁም መንግሥታዊና መንግስታዊ ያልሆኑ ተቋማት፣ የቢዝነስ ኮሚኒቲ እና የውጭ ዜጎች የሚሰጣቸውን አገልግሎቶች በግልጽ ለማሳወቅ፣ በተቀመጠው የአገልግሎት አሰጣጥ ስታንዳርድ መሰረት ለተገልጋዮች ቀልጣፋና ጥራት ያለው አገልግሎት ለመስጠት፣ የግልጽነትና የተጠያቂነት አሰራርን ለማረጋገጥ እንዲሁም ተገልጋዮች በኤምባሲው አገልግሎት አሰጣጥ ላይ አስተያየት፣ አቤቱታ፣ ቅሬታና ጥቆማ የሚሰጡበትን ሁኔታ በማመቻቸት የተገልጋዮችን እርካታ ለማረጋገጥ ነው፡፡

**4. የኤምባሲው ዕሴቶች**

- የሕዝብ አገልጋይነት (Public service)
- አጋርነት (Partnership)
- ተአማኒነት (Integrity)
- ሙያዊ ልህቀት (Professional Excellence)
- ቁርጠኝነት (Commitment)
- ውጤታማነት (Effectiveness)

**<u>የዕሴቶች መገለጫ</u>**

**4.1 <u>የሕዝብ አገልጋይነት (Public Service)</u>**

ኤምባሲው በተወከለባቸው ሀገሮች የሚኖሩ ኢትዮጵያዊያን፣ ትውልድ ኢትዮጵያዊያን እና ባለድርሻ አካላትን በትህትና፣ ቅንነትና ቅልጥፍና ማገልገል ኃላፊነታችንና ግዴታችን ነው፡፡ ይህም በየዕለቱ በምንሰጠው አገልግሎትና

በምናደርገው ዲፕሎማሲያዊ ተግባራችን የሚገለጽ ይሆናል፡፡ ይህ እሴታችን ለተገልጋዮች በምናስገኘው የእርካታ መጠን፣ እንዲሁም እያንዳንዱ አገልግሎት ለመስጠት ከወሰድነው ጊዜና ጥራት አንፃር የሚለካና በእለት ተዕለት እንቅስቃሴያችን ውስጥ ተግባራዊ የሚደረግ ይሆናል፡፡

### 4.2 አጋርነት (Partnership)

የተቋሙን ተልዕኮና ራዕይ በተሳካ ሁኔታ ተግባራዊ ለማድረግ የኤምባሲው ሠራተኞች እርስ በርሳችን፣ እንዲሁም ከሌሎች መንግሥታዊና መንግሥታዊ ካልሆኑ አካላትና የልማት አጋሮች ጋር በምንፈጥረው ወዳጅነትና የተቀናጀ አሰራር አጋርነትን እናጎለብታለን፡፡ አጋርነት የዕለት ተዕለት ሥራችን መገለጫ ሲሆን ይህም የመ/ቤቱን ራዕይ እና ተልዕኮ በማሳካት ሂደት ባፈራናቸው አጋሮች ብዛት የሚለካ ነው፡፡

### 4.3 ተዓማኒነት (Integrity)

የመንግሥት ፖሊሲዎችና ስትራቴጂዎችን በታማኝነትና በቁርጠኝነት መፈፀም፣ የሀገርንና የዜጎችን ጥቅም በከፍተኛ ተነሳሽነትና ቁርጠኝነት ማስጠበቅ እንዲሁም የአገርንና የተቋሙን ምስጢሮች መጠበቅ፣ ከአድልዎ የፀዳ ግልጽ አሠራር መዘርጋት፣ ፍትሐዊነት፣ ቅንነት፣ ግልጽነትና ተጠያቂነትን በሚያረጋግጥ አኳኋን የተቋሙን ተልዕኮና ኃላፊነት በብቃትና ውጤታማነት መወጣትን ይመለከታል፡፡ ይህም ሚሲዮኑ የሥራ ዕቅዶችንና ግቦችን ከመተግበርና ከማሳካት አኳያ የሚለካ ይሆናል፡፡

### 4.4 ሙያዊ ልህቀት (Professional Excellence)

የዲፕሎማሲ ሥራዎቻችንን በከፍተኛ ሙያዊ ብቃትና ክህሎት ማከናወንና ይህንንም በዕለት ተዕለት በምንፈጽማቸው የሥራ ውጤቶች ጥራት እንዲለካ ማድረግ፣ የተቋሙን ተልዕኮ በብቃት ለመፈፀም የሠራተኞች/የዲፕሎማቶች ሙያዊ ብቃትና ክህሎት ለማሳደግ ቀጣይነትና ጥራት ያላቸውን የሥልጠናና የአቅም ግንባታ ሥራዎችን በማከናወን የሚተገበር ይሆናል፡፡

### 4.5 ቁርጠኝነት (Commitment)

ፈጣንና ፍትሃዊ አገልግሎት ለማረጋገጥ፣ ዲሞክራሲያዊ ባህልን ለማጎልበት፣ መልካም አስተዳደርን ለማስፈን የዲፕሎማሲ ተግባራችንን ለመወጣት በቁርጠኝነት መፈፀም ወሣኝ ነው፡፡ በመሆኑም ተቋማዊ ኃላፊነታችንን ለመወጣት በየደረጃው ለሚካሄድ የዲፕሎማሲ ሥራ ቁርጠኛ አቋም መያዝ ከሁሉም የሚጠበቅ ይሆናል፡፡

### 4.6 ውጤታማነት (Effectiveness)

የዲፕሎማሲ ሥራችንንና አገልግሎት አሰጣጣችን በቅልጥፍና ከመስራት ባሻገር ሥራዎቻችንና አገልግሎቶቻችን ጥቅም የሚሰጡና ውጤት የሚያስመዘግቡ እንዲሆኑ ማድረግ ነው፡፡

## 5. የምንከተላቸው መርሆዎች

- ወቅታዊና አስተማማኝ መረጃ ለሁሉም ተደራሽ ማድረግ፣
- ቀልጣፋ፣ ጥራት ያለውና ደረጃውን የጠበቀ አገልግሎቶች መስጠት፣
- ላስቀመጥናቸው እሴቶች መገዛት፣
- ከአድሏዊ አሰራርና ከሥነ-ምግባር ጉድለት የፀዳ አሰራርን መከተል፣
- የተዘረጋውን የአሰራር ስርአት በየጊዜው በመፈተሽ ማሻሻል፣
- ለቅሬታዎችና አቤቱታዎች ፈጣን ምላሽ መስጠት፣ ገንቢ አስተያየቶችን በግብአትነት መጠቀም፣
- መልካም ተሞክሮዎችን ማስፋት፣

## 6. የኤምባሲው ተገልጋዮች

### 6.1 የውስጥ ተገልጋዮች

- የኤምባሲው ሰራተኞች

### 6.2 የውጭ ተገልጋዮች

6.2.1 በአገር ቤት

- የመንግስት የስራ ሀላፊዎች
- ለመንግስታዊ ስራ፣ ለጉብኝት፣ ለልምድ ልውውጥ፣ ለሴሚናር ወዘተ ወደ የምንሸፍናቸው አገሮች የሚመጡ የሴክተር መስሪያ ቤቶችና ተቋማት የልዑካን ቡድኖች፣
- የንግድ፣ የሙያ፣ የቢዝነስ ማህበራት ያካትታል፤

6.2.2 ኤምባሲው በተወከለባቸው አገራት

- ኢትዮጵያዊያን እና ትውልደ ኢትዮጵያዊያን፣
- ልዩ ልዩ የኮሙኒቲ እና የልማት ማህበራት፣
- የኢትዮጵያ ወዳጆች ማህበራት እና ድርጅቶች፣
- የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር መ/ቤቶች፣ ፓርላማዎች፣ መንግስታዊ ተቋማት፣ የትምህርትና ስልጠና ተቋማት፣
- የሚዲያ ተቋማትና ጋዜጠኞች፣
- ቲንክ ታንኮች እና የጥናትና ምርምር ተቋማት፣
- የንግድ ምክር ቤቶች፣ የቢዝነስ ማህበራት እና ኩባንያዎች፣
- መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች፣
- የተለያዩ አገራት ዜጎች፣
- የዲፕሎማቲክ ኮሚኒቲ አባላት፣

## 8. የተገልጋዮች መብት

- መረጃ በአካል፣ በስልክና በኢሜል ጠይቆ ማግኘት፣
- ሚሲዮኑ የሚሰጠውን አገልግሎት በተቀመጠው ስታንዳርድ መሰረት ማግኘት፣
- በአገልግሎት አሰጣጡ ላይ ያላቸውን ቅሬታና አቤቱታ በየደረጃው በማቅረብ ምላሽ ማግኘት፣
- መስተንግዶን ወይም አገልግሎት አሰጣጥን በተመለከተ ገንቢ አስተያየት መስጠት፣

## 9. ከተገልጋዮች የሚጠበቅ ግዴታ

- የሚፈለገውን አገልግሎት ለማግኘት የሚጠይቀውን መስፈርት ወይም ቅድመ ሁኔታ ማሟላት፣
- ትክክለኛነቱ የተረጋገጠ ሰነድ ወይም ማስረጃ ማቅረብ፣

## 10. ከኤምባሲው የሚጠበቁ ውጤቶች

- ለዜጎች እና ማህበራት የተጠበቁ መብቶችና ጥቅሞች፣
- ያደገ የዳያስፖራ ትስስርና ተሳትፎ፣
- በኢንቨስትመንት ፍሰት የተገኘ ተጨማሪ የውጭ ሃብት፣
- በተሰጠ አገልግሎት የጨመረ የተገልጋዮች እርካታ፣
- ለልማት፣ ሰላምና ዲሞክራሲ ሥርዓት ግንባታ ደጋፊ የውጭ ሁኔታ፣
- የተገነባ የሀገር ገጽታ፣
- የተደረገ የቴክኖሎጂ ሽግግር፣
- ሙያዊ ብቃት ያለውና ተልዕኮውን የሚፈጽም የሰው ኃይል፣

## 11. ለተገልጋዮች የምንገባው ቃል

- ግልጽነት፣ ሐቀኝነት እና ፍትሀዊነት የአሰራር ስርአትን የተከተለ አገልግሎት እንሰጣለን፣
- በታማኝነት፣ አለኝታነት፣ ተባባሪነት እና ተጠያቂነት እናገለግላለን፣

## 12. ተሳትፎና ግብአት

- አስተያየትና ጥቆማ መስጠት የሚፈልጉ ተገልጋዮች፡-
    - በአካል በመገኘት፣
    - በሚሲዮኑ ጽ/ቤት አስተያየት መስጫ ሳጥን በመጠቀም፣
    - በደብዳቤና በኢሜይል፣
    - በopen hour (በየሳምንቱ ረቡዕ ከ14:00 – 16:00)

* **የሚሲዮኑ አድራሻ:- Embassy of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, Stockholm**

**Birger Jarlsgatan 39**

**111 45 Stockholm**

**P.O.Box 10148, SE- 100 55**

**Stockholm, Sweden**

**Tel. No. +46812048500**

**Fax +4686609561**

**Email: ethemb.all@telia.com**

**Website: www.ethemb.se**

**Facebook: Embassy of Ethiopia, Stockholm**

**Twitter: Ethiopia in Sweden@ETHinSweden**

## 13. የቅሬታ አቀራረብ ስርዓት

### 13. 1 ዓላማ

የቅሬታ አቀራረብ ሥርዓት ዋና ዓላማ የሚሲዮኑ አገልግሎት አሰጣጥ ላይ ከተገልጋዮች የሚነሱ ቅሬታዎችን በመቀበል አስፈላጊውን የማስተካከያ እርምጃ በመውሰድ፣ ተጠያቂነትን በማስፈን የተገልጋይ እርካታን ለማስገኘት፣ የሚሲዮኑ ዲፕሎማቶችና የሎካል ሠራተኞች የአገልጋይነት መንፈስና የስራ ባህል ለማዳበር፣ መልካም አስተዳደር ለማስፈን እንዲሁም አጋርነትና ወዳጅነት በማፍራት የሚሲዮኑን ብሎም የአገራችንን መልካም ገጽታ ለመገንባት ነው፡፡

### 13.2 የቅሬታ አቀራረብ ሥርዓት

13.2.1 በአገልግሎት አሰጣጥ ላይ የሚቀርቡ አስተያየቶች፡-

- በሚሲዮኑ በሚሰጠው አጠቃላይ አገልግሎት፣ በእንግዳ አቀባበል፣ በመረጃ አሰጣጥ በመሳሰሉት ጉዳዮች አዎንታዊም ይሁን አሉታዊ አስተያየት ለዚሁ በተዘጋጀ ቅጽ ሊቀርብ ይችላል፣
- የቀረቡ አስተያየቶች በአስተዳደር ክፍል ተጠናቅሮ ለሚሲዮን መሪ ይቀርባል፤ የሚሲዮኑ መሪ ጉዳዩን በመመልከት ከቡድን አስተባባሪው ወይም ከሚመለከተው ፈጻሚ ጋር በመነጋገር የማስተካከያ እርምጃ ይወሰዳል፣

13.2.2 በግል የሚቀርቡ ቅሬታዎች

- ማንኛውም ተገልጋይ በተቀመጠው የአገልግሎት ቻርተር መሠረት አገልግሎት አልተሰጠኝም የሚል ቅሬታ ካለው ቅሬታውን በቅድሚያ አገልግሎቱን ለሰጠው ሠራተኛ ያቀርባል፣ ሠራተኛውም ቅሬታው ተገቢ ከሆነ ተቀብሎ ማስተካከያ ያደርጋል፣

- ተገልጋዩ በሠራተኛው በተሰጠ ማስተካከያ ያልረካና አገልግሎቱ በትክክል አልተሰጠኝም የሚል እምነት ካለው ጉዳዩን ለኮንሱላር ሀላፊ ወይም ለአስተዳደር ወይም ለሚሲዮኑ መሪ ማቅረብ ይችላል፣

### 13.2.3 ቅሬታ ምላሽ የሚያገኝበት ጊዜ

- የቀረቡ ቅሬታዎችን በመመርመር እንደ ቅሬታው ደረጃ እስከ ሦስት የሥራ ቀናት ባለው ጊዜ ምላሽ መሰጠት ይኖርባቸዋል፣

### 13.2.4. የማስተካከያ እርምጃዎች

- የሚሲዮኑ አገልግሎት ላይ የሚቀርቡ ቅሬታዎች አገልግሎቱን ማሻሻል የሚያስፈልግ መሆኑ ከታመነበት መመሪያን በጠበቀ መልኩ እንዲሻሻል ይደረጋል፣
- አገልግሎቱን በአግባቡ የማይሰጥ ሠራተኛ ላይ በመመሪያው መሠረት እርምጃ ይወሰዳል፣
- ያለ አግባብና ያለበቂ ምክንያት ቅሬታ የሚያቀርብ አካል/ግለሰብ ያቀረበው ቅሬታ ትክክል አለመሆኑን እንዲያውቀው ይደረጋል፣

## 14. የመረጃ ማስተላለፊያ መንገዶች

### 14.1 በሚሲዮኑ የሚሰጡ መረጃዎች

- የኮንሱላር አገልግሎት መረጃዎች
- የኢንቨስትመንት ቢዝነስና ቱሪዝም መረጃዎች
- የዲያስፖራ መረጃዎች
- ልዩ ልዩ የሚዲያ መረጃዎች

### 14.2 የመረጃ ማስተላለፊያ መንገዶች

- በመረጃ ዴስክ
- በዲያስፖራ መድረኮች
- በብሮሸር
- በኢሜይል
- በሚሲዮኑ ድረ-ገጽና ሶሻል ሚዲያዎች (facebook, twitter)
- በሚሲዮኑ Online መጽሔት

## 15. የክትትልና ግምገማ ሥርዓት

- ወቅታዊ ሪፖርት ግምገማ፣
- ግብረ-መልስ አሰጣጥ፣
- የተገልጋይ እርካታ ሰርቬይ ውጤት፣
- የአገልግሎት ቻርተር አፈፃፀም ክትትልና ግምገማ

# የስቶክሆልም ኤምባሲ የአገልግሎት ቻርተር

| ተ.ቁ | የሚሰጡ አገልግሎቶች | የአገልግሎት አሰጣጥ ስታንዳርድ | | | አገልግሎቱን ለማግኘት የሚጠበቅ ቅድመ ሁኔታ | ምርመራ<br>የአገልግሎት ክፍያ<br>(በSEK) |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ጊዜ | ጥራት | ወጪ | | |
| **1. በኢኮኖሚና ቢዝነስ ማስፋፊያ ዘርፍ የሚሰጡ አገልግሎቶች** | | | | | | |
| 1 | የኢንቨስትመንት፣ ቢዝነስ፣ ንግድና ቱሪዝም መረጃዎች ለተጠቃሚዎች መስጠት፣ | መረጃው በሚሲዮኑ ካለ 1 ሰዓት ከአገር ቤት ተጠይቆ የሚቀርብ ከሆነ ከ5-7 ቀን | የተሟላ መረጃ የያዘ አገልግሎት | | • መረጃ የሚፈልጉ አካላት በኢ-ሜይል፣ በስልክ፣ በአካልና በደብዳቤ መጠየቅ | |
| 2 | በቢዝነስ ኤግዚቢሽኖችና የንግድ ትርኢቶች ላይ ለሚደረግ ተሳትፎና የፕሮሞሽን ስራዎች ድጋፍ መስጠት | እንደ ዝግጅቱ የቆይታ ጊዜ | ለውጤታማ ተሳትፎ የተደረገ ፋሲሊቴሽን | ለኤግዚቢሽን በሚመደብ በጀት | • የድርጅቱ ፕሮፋይል እና ህጋዊነት ሰነድ<br>• የተሳትፎ / የግብዣ ደብዳቤና ኤግዚብሽኑን የተመለከተ መረጃ<br>• ከንግድ ም/ቤት ወይም ከማህበራት የድጋፍ ደብዳቤ | |
| 3 | በተወከልንባቸው አገራት የሚገኙ ኩባንያዎች/ባለሀብቶች በአገራችን ለሚያደርጉት የቅድመ ኢንቨስት መንት ጉብኝት ፕሮግራማቸውን ማመቻቸት፣ | ከ3 – 5 ቀን | የተሳካ የጉብኝት ፕሮግራም | | • የኩባንያው የተሟላ ፕሮፋይል እና የኢንቨስትመንት መስክ ፍላጎት ዝርዝር መረጃ<br>• በቅድመ ኢንቨስትመንት ጉብኝት ሊያነጋግሩ የሚፈልጉት መ/ቤት፣ የሚሄዱበት ጊዜ እና የልዑካን ቡድን አባላት መረጃ | |
| 4 | የአገራችን አምራቾችና የንግድ ድርጅቶች በተወከልንባቸው አገራት ለሚያካሂዱት የገበያ ጥናትና ምርቶቻቸውን የማስ ተዋወቅ እንቅስቃሴ ድጋፍ መስጠት፣ | ጥያቄው በቀረበ በአንድ ሳምንት ጊዜ | የተሰጠ የተሟላ ድጋፍ | | • የአምራች ድርጅት ፕሮፋይል፣ የድርጅቱን ህጋዊነት የሚገልጽ ሰነድ፣ የላኪነት ፈቃድ፣ የምርት ጥራት ማረጋገጫ፣ Certificate of Origin<br>• የድርጅቱን ምርቶች የሚያስተዋወቅበት ሀገሮች እና የቢዝነስ ድርጅቶች መረጃ<br> | |

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 5 | በተወከልንባቸው አገራት የሚገኙ ቱር ኦፐሬተሮች በአገራችን ለሚያደርጉት Fam-trip አስፈላጊውን ድጋፍ መስጠት፣ | 3 ቀን | የተሰጠ የተሟላ ድጋፍ | | • የኩባንያው የተሟላ ፕሮፋይልና ጉብኝቱን የተመለከተ መረጃ | |
| 6 | ለውጭ ምርቶቻችን የገበያ ትስስር እንዲፈጠርላቸው ለሚጠይቁ አምራቾች/አቅራቢዎች ገዥዎች እንዲያገኙ ድጋፍ ማድረግ፣ | 1 ወር | የተፈጠረ የገበያ ትስስር | | • ምርቱን የሚያስተዋውቅና ገበያ የሚፈለግለትን አገር የሚገልጽ መረጃ<br>• የላኪ ድርጅት ፕሮፋይል፣ የድርጅቱን ሕጋዊነት የሚገልጽ ሰነድ፣ የላኪነት ማረጋገጫ ማስረጃ፣ የምርት ስሪት ሀገር፣ ሰርትፍኬት እንዲሁም ናሙና | |
| 7 | ለዕውቀትና ቴክኖሎጂ ሽግግር ከውጭ ተቋማት ጋር ግንኙነት መፍጠር ለሚፈልጉ አካላት ተገቢውን ድጋፍ መስጠት፣ | 1 ወር | ተቋሙ የፈጠረው ግንኙነት | | • የጥያቄ አቅራቢው መ/ቤት/ ድርጅት/ ተቋም ፕሮፋይልና contact person መረጃ<br>• ቴክኖሎጂው የሚጠየቅበት አገርና ተቋም/ኩባንያ፣ የሚፈለገው ቴክኖሎጂ ዝርዝር መረጃ (specification) | |
| 8 | የአገራችን ቱር ኦፐሬተሮች ከውጭ ቱር ኦፐሬተሮች ጋር እንዲጎዳኙ ለሚቀርብ ጥያቄ ድጋፍ መስጠት፣ | 1 ወር | የተፈጠረ ጉድኝት | | • የድርጅቱን ፕሮፋይልና ሕጋዊነት የሚገልጽ ሰነድ<br>• ከባሕልና ቱሪዝም ሚኒስቴር/ከማህበሩ የድጋፍ ደብዳቤ | |
| 9 | ኩባንያዎች/ባለሀብቶች በኢንቨስትመንትና ቢዝነስ የሥራ እንቅስቃሴ የሚያጋጥሙአቸውን ችግሮች ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በመሆን መፍታት፣ | ከ15 ቀን እስከ 1 ወር | የተፈታ ማነቆ | | • ችግር ያጋጠመው ኩባንያ ሙሉ ስም፣ አድራሻ፣ የተሰማራበት የሥራ መስክ፣ ያሉ ውሎችና ስምምነቶች መረጃ<br>• ያጋጠመውን ችግር በዝርዝር በመግለጽ ችግሩ እንዲፈታለት በኢሜይል፣ በስልክ ወይም በአካል ማቅረብ፣<br>• ችግር ያደረሰውን ወገን የተመለከተ መረጃ ማቅረብ፣ እንዲሁም ችግሩን ለመፍታት የተደረገ ግንኙነት ካለ መረጃውን ማያያዝ፣ | |

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 10 | በውጭ አገር የተመሰረተ መንግስታዊ ያልሆነ ድርጅት ( NGO ) በአገራችን ገብቶ ለመስራት ለሚያቀርበው ጥያቄ ተገቢ አገልግሎት መስጠት | 1 ቀን | ተጣርቶ የተረጋገጠ የተሟላ ሰነድ መላኩ | | • የበጎ አድራጎት ድርጅት መቋቋሙን የሚያሳይ በአገሩ የተሰጠ የተረጋገጠ የምስክር ወረቀት<br>• የበጎ አድራጎት ድርጅቱ የተረጋገጠ የመተዳደሪያ ደንብ<br>• ድርጅቱ ኢትዮጵያ ውስጥ ገብቶ እንቅስቃሴ እንዲያደርግ የድርጅቱ አመራር ቦርድ የተስማማበት የተረጋገጠ ደብዳቤ<br>• የድርጅቱ ዋና ጽ/ቤት ከሚገኝበት አገር የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ወይም መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችን ጉዳይ ከሚከታተል አካል የተሰጠ የድጋፍ ደብዳቤ<br>• ድርጅቱ ኢትዮጵያ ውስጥ ገብቶ ለመስራት ያቀደውን ተግባር የተመለከተ ፕሮጀክት እና የወጪ ዝርዝር መረጃ<br>• የድርጅቱን በጀት ከጠቅላላ በጀቱ ከ70 በመቶ የማያንስ ለአላማው ማስፈጸሚያ እና ከ30 በመቶ ያልበለጠ ለአስተዳደራዊ ወጪ ለማዋል በሚያስችል መልኩ የተዘጋጀ ሰነድ<br>• በኢትዮጵያ ድርጅቱን ወክሎ ለሚሰራ አካል የተሰጠ የተረጋገጠ ህጋዊ ደብዳቤ<br>• የድርጅቱ ተወካይ የተረጋገጠ ህጋዊ የትምህርት ማስረጃ (ቢያንስ ዲፕሎማ) እና የማንነት ማስረጃ (CV) | |
| **2. በቆንስላ ጉዳዮች ዘርፍ የሚሰጡ አገልግሎቶች** | | | | | | |
| 1 | የአዲስ ፓስፖርት አገልግሎት (በውጭ አገር ለተወለዱ ህጻናት) | ከ20 - 40 ደቂቃ | ትክክለኛና የተሟላ ሰነድ መቅረቡ | | • የወላጅ የጸና (valid) የኢትዮጵያ ፓስፖርት ቅጂ<br>• የሚኖርበት አገር የምዝገባ ማስረጃ<br>• የተሞላ ማመልከቻ ፎርም<br>• በወላጅ በሁለት ኮፒ የተሞላ የህጻናት ማመልከቻ ፎርም<br>• አራት 3x4 የሆነ ከለር ፎቶግራፍ (መደቡ ነጭ)<br>• የአገልግሎት ክፍያ | **522 SEK** |

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 2 | የፓስፖርት ዕድሳት አገልግሎት | ከ20 - 45 ደቂቃ | ትክክለኛና የተሟላ ሰነድ መቅረቡ | | • የኢትዮጵያ ፓስፖርት ዋናውና ቅጂው<br>• የሚኖርበትን አገር የሚገልጽ ማስረጃ<br>• ለትምህርት የመጣ ከሚማርበት ተቋም መደበኛ ተማሪ መሆኑን የሚገልጽ ማስረጃ<br>• የተሞላ ማመልከቻ ፎርም<br>• ዕድሜው 14 እና በላይ ከሆነ አሻራ መስጠት<br>• ሶስት 3x4 የሆነ ከለር ፎቶግራፍ (መደቡ ነጭ)<br>• የአገልግሎት ክፍያ | **522 SEK** |
| 3 | ለጠፋ ወይም ለተበላሸ ፓስፖርት ምትክ አገልግሎት | ከ30 - 45 ደቂቃ | ትክክለኛና የተሟላ ሰነድ መቅረቡ | | • የቀድሞ ፓስፖርት ቅጂ<br>• የሚኖርበት አገር የምዝገባ ማስረጃ<br>• መጥፋቱን የሚያረጋግጥ የፖሊስ ማስረጃ<br>• በሁለት ኮፒ የተሞላ ፎርም<br>• አራት 3x4 የሆነ ከለር ፎቶግራፍ (መደቡ ነጭ)<br>• የአገልግሎት ክፍያ | **783 SEK** |
| 4 | የይለፍ ሰነድ (ሊሴ ፓሴ) አገልግሎት | ከ20 - 45 ደቂቃ | የተሟላ ሰነድ መቅረቡ | | • በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር የተረጋገጠ የልደት ማስረጃ፣ወይም ኢትዮጵያዊነቱን የሚገልጽ ከውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር የተጻፈ ደብዳቤ<br>• የሚኖርበት አገር የምዝገባ ማስረጃ<br>• በሁለት ኮፒ የተሞላ ፎርም<br>• አራት 3x4 የሆነ ከለር ፎቶግራፍ (መደቡ ነጭ)<br>• በአካል መቅረብ ለማይችሉ ከሚኖሩበት አገር በፖሊስ የተረጋገጠ የጣት አሻራ<br>• የአገልግሎት ክፍያ | **783 SEK** |

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 5 | ሰነድ ማረጋገጥ አገልግሎት | ከ20 - 45 ደቂቃ | ትክክለኛ ሰነድ መቅረቡ | | • ከኢትዮጵያ የመነጨ ዜግነትን የሚገልጽ የተረጋገጠ ማስረጃ<br>• የቀድሞ የኢትዮጵያ ፓስፖርት ወይም ቅጂ፣ ወይም<br>• በውጭ ጉዳይ የተረጋገጠ የልደት ማስረጃ<br>• የሚኖርበት አገር የምዝገባ ማስረጃ<br>• የተሞላ ማመልከቻ ፎርም<br>• የአገልግሎት ክፍያ | **514 SEK**<br>**ለኢትዮጵያውያንና ትውልድ ኢትዮጵያውያን**<br>**783 SEK**<br>**ለውጭ አገር ዜጎች** |
| 6 | አዲስ የትውልድ ኢትዮጵያ መታወቂያ ካርድ አገልግሎት<br>• ዕድሜያቸው ከ18 አመት በላይ ለሆኑ | ከ30 -50 ደቂቃ | የተሟላ ሰነድ መቅረቡ | | • የቀድሞ የኢትዮጵያ ፓስፖርት ዋናውና ሁለት ቅጂ ፤ ወይም<br>• በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር የተረጋገጠ የልደት ሰርትፍኬት፣ ወይም<br>• ዜግነቱ በፍርድ ቤት የተረጋገጠና ማስረጃው በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር authenticate የተደረገ ፤ወይም<br>• የጉዲፈቻ ማስረጃ ህጋዊነት በፍርድ ቤት የተረጋገጠና በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር authenticate የተደረገ ፤ወይም<br>• በፍርድ ቤት የተረጋገጠና በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር authenticate የተደረገ የቤተሰብ የንብረት ውርስ ማስረጃ<br>• የሚኖርበት አገር የምዝገባ ማስረጃ<br>• ዜግነት ከወሰደበት አገር የተሰጠው የጸና (ከ6 ወር ያላነሰ ጊዜ ያለው) ፓስፖርት<br>• የተሞላ መጠየቂያ ፎርም<br>• ሶስት 3x4 የሆነ ከለር ፎቶግራፍ (መደቡ ነጭ)<br>• የጣት አሻራ መስጠት፣ በፖስታ ለሚልኩ በፖሊስ የተረጋገጠ የጣት አሻራ<br>• የአገልግሎት ክፍያ | 1740 SEK |

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | • ለህጻናት<br>(ዕድሜያቸው ከ18 አመት<br>በታች ለሆኑ) | ከ30 - 50<br>ደቂቃ | የተሟላ ሰነድ<br>መቅረቡ | | • ዜግነት የወሰደበት አገር የጸና (valid) ፓስፖርት ዋናውና ቅጂ<br>• የሚኖርበት አገር የምዝገባ ማስረጃ<br>• በተወለደበት አገር የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር የተረጋገጠ የልደት ማስረጃ<br>• የወላጅ የታደሰ የትውልድ ኢትዮጵያ መታወቂያ ዋናውና ቅጂ<br>• የቀድሞ የወላጅ የኢትዮጵያ ፓስፖርት ወይም በውጭ ጉዳይ የተረጋገጠ የልደት ማስረጃ<br>• ከ14 አመት በላይ የሆነ የጣት አሻራ መስጠት<br>• በሁለት ኮፒ የተሞላ መጠየቂያ ፎርም<br>• 3x4 የሆነ ሶስት ከለር ፎቶግራፍ (መደቡ ነጭ)<br>• የአገልግሎት ክፍያ | **174 SEK** |

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 7 | የትውልድ ኢትዮጵያ መታወቂያ ካርድ እድሳት አገልግሎት | ከ30 - 45 ደቂቃ | የተሟላ ሰነድ መቅረቡ | | • የኢትዮጵያ ፓስፖርት ዋናውና ሁለት ቅጂ<br>• የትውልድ ኢትዮጵያዊ መታወቂያ<br>• በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር የተረጋገጠ የልደት ሰርትፍኬት ወይም<br>• ዜግነቱ በፍርድ ቤት የተረጋገጠና ማስረጃው በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር authenticate የተደረገ ወይም<br>• የጉዲፈቻ ማስረጃ ህጋዊነት በፍርድ ቤት የተረጋገጠና ማስረጃው በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር authenticate የተደረገ ወይም<br>• በፍርድ ቤት የተረጋገጠና በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር authenticate የተደረገ የቤተሰብ የንብረት ውርስ ማስረጃ<br>• የሚኖርበት አገር የምዝገባ ማስረጃ<br>• ዜግነት ከወሰደበት አገር የተሰጠው የጸና (valid) ፓስፖርት<br>• የተሞላ የዕድሳት መጠየቂያ ፎርም<br>• ሶስት 3x4 የሆነ ከለር ፎቶግራፍ (መደቡ ነጭ)<br>• የጣት አሻራ መስጠት፣ በፖስታ ለሚልኩ በፖሊስ የተረጋገጠ የጣት አሻራ<br>• የአገልግሎት ክፍያ | 1740 SEK |

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 8 | የጠፋ ወይም የተበላሸ የትውልደ ኢትዮጵያዊ መታወቂያ ካርድ ምትክ አገልግሎት | ከ30 - 45 ደቂቃ | የተሟላ ሰነድ መቅረቡ | | • የቀድሞ የኢትዮጵያ ፓስፖርት ዋናውንና ሁለት ቅጂ<br>• በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር የተረጋገጠ የልደት ሰርትፍኬት ወይም<br>• ዜግነቱ በፍርድ ቤት የተረጋገጠና ማስረጃው በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር authenticate የተደረገ ወይም<br>• የጉዲፈቻ ማስረጃ ህጋዊነት በፍርድ ቤት የተረጋገጠና ማስረጃው በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር authenticate የተደረገ ወይም<br>• በፍርድ ቤት የተረጋገጠና በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር authenticate የተደረገ የቤተሰብ የንብረት ውርስ ማስረጃ<br>• የሚኖርበት አገር የምዝገባ ማስረጃ<br>• ዜግነት ከወሰደበት አገር የተሰጠው የጸና (valid) ፓስፖርት<br>• የፖሊስ ማስረጃ<br>• የተሞላ መጠየቂያ ፎርም<br>• ሶስት 3x4 የሆነ ከለር ፎቶግራፍ (መደቡ ነጭ)<br>• የጣት አሻራ መስጠት፣በፓስታ ለሚልኩ በፓሊስ የተረጋገጠ የጣት አሻራ<br>• የአገልግሎት ክፍያ | **1992 SEK** |
| 9 | የቱሪስት ቪዛ አገልግሎት<br>(በፖስታ መላላክ ብቻ የሚሰጥ)<br>• የ30 ቀን ቪዛ (single)<br>• የ90 ቀን ቪዛ (single)<br>• የ90 ቀን ቪዛ (multiple)<br>• የ180 ቀን ቪዛ (multiple) | ፖስታው በደረሰ ከ1 - 2 ቀን ውስጥ ሰርቶ መመለስ | ሰነዶች ያለ ስህተት መዘጋጀታቸው | | • የተሞላ ማመልከቻ ፎርም<br>• ከምንወክለው አገር ያገኘው የጸና (ቢያንስ የ6 ወር ጊዜ ያለው) ፓስፖርት<br>• 3x4 የሆነ አንድ ከለር ፎቶግራፍ (መደቡ ነጭ)<br>• የአገልግሎት ክፍያ | **348 SEK (ለ1 ወር)**<br>**522 SEK ለ3 ወር (single)**<br>**609 SEK ለ3 ወር (multiple)**<br>**696 SEK ለ6 ወር (multiple)** |

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 10 | የስራ ቪዛ አገልግሎት ለኢንቨስትመንት/ ቢዝነስ (IV)<br><br>◆ **ለኢንቨስትመንት የሚሄዱ በአካል ከመጡ ይስተናገዳሉ** | ፖስታው በደረሰ በአንድ ቀን ውስጥ ሰርቶ መመለስ፣<br><br>በአካል ከመጡ በዕለቱ ይስተናገዳሉ | ሰነዶች ያለ ስህተት መዘጋጀታቸው | | • የተሞላ ማመልከቻ ፎርም ከአንድ ከለር ፎቶግራፍ ጋር<br>• ዜግነት ከወሰደበት አገር ያገኘው የጸና (valid) ፓስፖርት<br>• ጉዳዩን የሚገልጽ ለኤምባሲያችን በአድራሻ የተጻፈ ደብዳቤ<br>• የአገልግሎት ክፍያ | **261 SEK (ለ1 ወር)**<br>**348 SEK (ለ3 ወር multiple)**<br>**522 SEK (ለ6 ወር multiple)**<br>**1044 SEK (ለአንድ አመት)** |
| | ለመንግስታዊ ስራዎች (GIV)<br><br>◆ **ለመንግስታዊ ስራ የሚሄዱ በአካል ከመጡ ይስተናገዳሉ** | ፖስታው በደረሰ ከ1 - 2 ቀን ውስጥ ሰርቶ መመለስ፣ | ሰነዶች ያለ ስህተት መዘጋጀታቸው | | • የተሞላ ማመልከቻ ፎርም ከአንድ ከለር ፎቶግራፍ ጋር<br>• ዜግነት ከወሰደበት አገር ያገኘው የጸና (valid) ፓስፖርት<br>• ጉዳዩን የሚገልጽ ለኤምባሲያችን በአድራሻ የተጻፈ ደብዳቤ<br>• የአገልግሎት ክፍያ | **174 SEK (ለ1 ወር)**<br>**696 SEK (ለ3 ወር multiple)**<br>**1044 SEK (ለ6 ወር multiple)** |
| | ለጋዜጠኛ/ ለሚዲያ ሰራተኛ (JV) (ለአንድ ወር) | 15 የስራ ቀናት | ሰነዶች ያለምንም ስህተት መዘጋጀቱ | | • የተሞላ ማመልከቻ ፎርም ከአንድ ከለር ፎቶግራፍ ጋር<br>• ዜግነት ከወሰደበት አገር ያገኘው የጸና (ከ6 ወር ያላነሰ ጊዜ ያለው) ፓስፖርት<br>• ከሚሰራበት ተቋም የጉዞውን ዓላማ የሚገልጽ ደብዳቤ<br>• ለሚዲያ ስራ የሚጠቀማቸው ዕቃዎች ዝርዝር<br>• ቪዛው ሲፈቀድ የአገልግሎት ክፍያ | **348 SEK** |

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | **ልዩ ልዩ ቪዛዎች አገልግሎት**<br>• ለውጭ ኩባንያ/ኢንተርፕራይ ተቀጣሪ (WV)<br>• ለመንግስት መስሪያ ቤት ተቀጣሪ (GV)<br>• ለአህጉራዊ እና አለምአቀፍ ድርጅት ተቀጣሪ (RI)<br>• ለመንግስታዊ ያልሆነ ድርጅት (NGO) ተቀጣሪ (NV)<br>• ለአጭር ጊዜ ሴሚናር፣ ወርክሾፕ፣ስብሰባ (CV)<br>• ለግል ድርጅት ተቀጣሪ (PE) | ፖስታው በደረሰ በ2 ቀን ውስጥ ሰርቶ መመለስ፣ | ሰነዶች ያለ ስህተት መዘጋጀታቸው | | • ከኢትዮጵያ ኢሚግሬሽን የተፈቀደ የስራ ቪዛ<br>• ከጋባዥ ድርጅት የተጻፈ የግብዣ ደብዳቤ<br>• የተሞላ መጠየቂያ ፎርም ከአንድ ከለር ፎቶግራፍ ጋር<br>• ዜግነት ከወሰደበት አገር ያገኘው የጸና (ከ6 ወር ያላነሰ ጊዜ ያለው) ፓስፖርት<br>• የአገልግሎት ክፍያ | **WV**<br>**348 SEK (ለ1 ወር)**<br>**522 SEK (ለ3 ወር single)**<br>**696 SEK (ለ3 ወር multiple)**<br>**GV**<br>**261 SEK (ለ1 ወር)**<br>**348 SEK (ለ3 ወር single)**<br>**522 SEK (ለ3 ወር multiple)**<br>**RI**<br>**435 SEK (ለ1 ወር)**<br>**609 SEK (ለ3 ወር single)**<br>**783 SEK (ለ3 ወር multiple)**<br>**NV**<br>**522 SEK (ለ1 ወር)**<br>**CV**<br>**261 SEK (ለ1 ወር)**<br>**PE**<br>**261 SEK (ለ1 ወር)**<br>**435 SEK (ለ3 ወር single)**<br>**696 SEK (ለ3 ወር multiple)** |

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 11 | ዲፕሎማቲክ ቪዛ / ሰርቪስ ቪዛ አገልግሎት | ፖስታው በደረሰ ከ1 - 2 ቀን ውስጥ ሰርቶ መመለስ፣ | ሰነዶች ያለ ስህተት መዘጋጀታቸው | | • ከውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ወይም ከኤምባሲ የተጻፈ ኖት ቨርቫል<br>• የጸና (ከ6 ወር ያላነሰ ጊዜ ያለው) ፓስፖርት<br>• የተሞላ ማመልከቻ ፎርም<br>• 3x4 የሆነ አንድ ከለር ፎቶግራፍ (መደቡ ነጭ) | ግራቲስ |
| 12 | የትራንዚት ቪዛ አገልግሎት<br>• 12 ሰዓት የሚቆይ<br>• 24 ሰዓት የሚቆይ<br>• 48 ሰዓት የሚቆይ<br>• 72 ሰዓት የሚቆይ<br>• ለ2 ቀን ትራንዚት (በ24 ሰዓት ውስጥ) | ፖስታው በደረሰ በ2 ቀን ውስጥ ሰርቶ መመለስ፣ | ሰነዶች ያለ ስህተት መዘጋጀታቸው | | • የተሞላ ማመልከቻ ፎርም<br>• 3x4 የሆነ አንድ ከለር ፎቶግራፍ (መደቡ ነጭ)<br>• ከምንወክላቸው አገሮች ያገኘው የጸና (ከ6 ወር ያላነሰ ጊዜ ያለው)ፓስፖርት<br>• የሚሄድበት አገር የመግቢያ ቪዛ እና ትኬት ያለው<br>• የአገልግሎት ክፍያ | **218 SEK (12 ሰዓት)**<br>**348 SEK (24 ሰዓት)**<br>**435 SEK (48 ሰዓት)**<br>**522 SEK (72 ሰዓት)**<br>**435 SEK (ለ2 ቀን)** |
| 13 | የፍርድ ቤት ውሳኔዎችና ሀብት ነ ጉዳዮችን ሰነድ ማረጋገ አገልግሎት፣<br>• **ለኢትዮጵያውያንና ትውልደ ኢትዮጵያውያን** | ከ30-45 ደቂቃ | በስታንዳርዱ መሠረት በፍጥነ መስተናገዱ | | • የጸና የኢትዮጵያ ፓስፖርት ዋናውና ቅጂ፣ ወይም የጸና የትውልደ ኢትዮጵያዊ መታወቂያ ካርድ<br>• የጸና የመኖሪ ያፈቃድ / የስራ ፈቃድ / የሚኖርበት አገር የምዝገባ ማስረጃ ኮፒ<br>• በአግባቡ የተዘጋጀ የውክልና ሰነድ<br>• የአገልግሎት ክፍያ<br>• ከዚህ በተጨማሪ በፖስታ ቤት ለሚሰጥ የውክልና አገልግሎት ወካይ በአካባቢው በሚገኝ የሰነድ ምዝገባ ተቋም (Notary Public) በአካል በመቅረብ የፈረመበት እና የተረጋገጠ የውክልና ሰነድ ማያያዝ፣ | **540 SEK** |

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 14 | • **ለውጭ ዜጎች** | ከ30-45 ደቂቃ | በስታንዳርዱ መሠረት በፍጥነት መስተናገዱ | | • ዜግነቱን የሚያረጋግጥ የጸና ፓስፖርት ዋናውና ቅጂ፣<br>• በአገሩ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር የተረጋገጠ ሰነድ<br>• የአገልግሎት ክፍያ<br>• አገልግሎቱን በውክልና ለሚያስፈጽሙ አካላት የውክልና ስልጣን ወይም የጉዳይ ፈጻሚ ህጋዊ ፈቃድ ማያያዝ | **827 SEK** |
| 15 | የአስከሬን መሸኛ አገልግሎት | 1 ሰዓት | በፍጥነት መስተናገዱ | | • የሟችን ዜግነት የሚያረጋገጥ ማስረጃ<br>• የሚኖርበትን አገር የሚገልጽ ማስረጃ<br>• የሆስፒታል ማስረጃ (Death Certificate)<br>• በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር የተረጋጋጠ የጉዞ ሰርትፍኬት | ------------------- |
| 16 | የትብብር ድጋፍ ደብዳቤ አገልግሎት | ከ20 - 40 ደቂቃ | በስታንዳርዱ መሠረት በፍጥነት መስተናገዱ | | • የኢትዮጵያ ፓስፖርት/ የትውልድ ኢትዮጵያዊ መታወቂያ ካርድ (ስድስት ወር ያላነሰ ጊዜ ያለው)<br>• ከሚኖርበት አገር የምዝገባ ማስረጃ<br>• ዜግነት ከወሰደበት አገር የተሰጠው ፓስፖርት (ስድስት ወር ያላነሰ ጊዜ ያለው)<br>• የተሞላ የማመልከቻ ፎርም<br>• ሶስት 3x4 የሆነ ከለር ፎቶግራፍ (መደቡ ነጭ) | .................................. |
| 17 | በቆንስላ ጉዳዮች ዙሪያ በስልክ፣በኢሜይል፣በግንባር ቀርበው መረጃ ለሚጠይቁ የሚሰጥ አገልግሎት | 5 ደቂቃ (ለስልክ)<br>10 ደቂቃ (በግንባር)<br>በዕለቱ (ለኢሜይል) | በወቅቱ ምላሽ መሰጠቱ | | • በተወከልንባቸው አገሮች የሚኖሩ ተገልጋዮች የሚፈልጉትን መረጃ በግልጽ ባጭሩ ማቅረብ | ---------------- |
| **3. በዳያስፖራ ዘርፍ የሚሰጡ አገልግሎቶች** | | | | | | |
| 1 | ለኢትዮጵያዊያንና ትውልድ ኢትዮጵያዊያን መረጃና የማማከር አገልግሎት መስጠት | 15 ደቂቃ | ተገቢው መረጃ መሰጠቱ | | • የሚፈልጉትን የመረጃና የምክር አገልግሎት ጥያቄ በአካል፣ በስልክ እና በኢ-ሜይል ማቅረብ፣ | |
| 2 | በኢንቨስትመንትና ቢዝነስ | | ፈጣን ምላሽ | | • የፀና ፓስፖርት/ የትውልድ ኢትዮጵያዊ መታወቂያ ካርድ | |

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | ለሚሳተፉ የዳያስፖራ አባላት ተገቢውን ድጋፍ መስጠት | ከ30-45 ደቂቃ | መሰጠቱ | | እና የመኖሪያ ፈቃድ ቅጂ<br>• የድጋፍ ደብዳቤ ጥያቄ<br>• የሚሰማሩበት ኢንቨስትመንት ፕሮጀክት ፕሮፖዛል ወይም ቢዝነስ ፕላን | |
| 3 | በኢንቨስትመንትና ቢዝነስ መስኮች ለመሰማራት ፈቃድ ላወጡ በፍራንኮ ቫሉታ ማሽነሪዎችን እንዲያስገቡ ድጋፍ መስጠት | ከ30-45 ደቂቃ | ተገቢው ድጋፍ መሰጠቱ | | • የፀና የፓስፖርት / የትውልድ ኢትዮጵያዊ መታወቂያ ካርድ እና የመኖሪያ ፈቃድ ቅጂ<br>• የኢንቨስትመንት ፈቃድ ቅጂ<br>• የሚያስገቧቸው ማሽነሪዎች አይነት ዝርዝር መረጃ<br>• የድጋፍ ደብዳቤ ጥያቄ | |
| 4 | በዕውቀትና ቴክኖሎጂ ሽግግር ለሚሳተፉ የዲያስፖራ ሙያተኞች ድጋፍ መስጠት | ከ5-7 ቀን | ተገቢ ተቋማት መመቻቸቱ | | • የፀና የፓስፖርት/ የትውልድ ኢትዮጵያዊ መታወቂያ ካርድ እና የመኖሪያ ፈቃድ ቅጂ<br>• የትምህርትና የስራ ልምድ ታሪክ ወይም CV እና የትምህርት ማስረጃ<br>• የቴክኖሎጂውን ምንነትና ለአገራችን ያለውን ጠቀሜታ የሚገልጽ ማስታወሻ (Concept Note) | |
| 5 | በአገር ውስጥ ባንኮች የውጭ ምንዛሪ ተቀማጭ ሂሳብ ለሚከፍቱ የዲያስፖራ አባላት አገልግሎት መስጠት | ከ20-30 ደቂቃ | የተሟላ ሰነዶች መላኩ | | • የፀና ፓስፖርት / የትውልድ ኢትዮጵያዊ መታወቂያ ካርድ እና የመኖሪያ ፈቃድ ቅጂ<br>• የተሞላና በሂሳብ ከፋቹ የተፈረመ የማመልከቻ ቅጽ<br>• አንድ የፓስፖርት መጠን ያለው ባለቀለም ፎቶግራፍ (በነጭ መደብ) | |

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 6 | ለጋራ መኖሪያ ቤት ልማት ፕሮግራም ተመዝጋቢዎች አገልግሎት መስጠት | 1 ሰዓት | ፈጣን መስተንግዶ መሰጠቱ | | • የፀና የፓስፖርት/ የትውልድ ኢትዮጵያዊ መታወቂያ ካርድ እና የመኖሪያ ፈቃድ ዋናውና ቅጂው<br>• ሁለት ፓስፖርት መጠን ባለቀለም ፎቶግራፍ<br>• የተሞላ የምዝገባ ቅጽ<br>• በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ የግል የውጭ ምንዛሪ ባንክ ሂሳብ በመክፈት የቤቱን ግንባታ ወጪ 50% በውጭ ምንዛሪ (በዶላር፣ዩሮ፣ፓውንድ) በማስቀመጥ ይህንኑ የሚያረጋግጥ ደረሰኝ ቅጂ ማቅረብ<br>• ያገባ/ች የተረጋገጠ የጋብቻ ሰርትፍኬት ወይም ያላገባ/ች ማስረጃ ዋናው ቅጂው<br>• በማህበር ለተደራጁ የማህበሩ አባላት በሙሉ የፈረሙበት የመመስረቻ ቃለ-ጉባኤ እና የማህበሩ መተዳደሪያ ደንብ | |
| 7 | የታላቁ ህዳሴ ግድብ ቦንድ ሽያጭ አገልግሎት መስጠት | ከ10-15 ደቂቃ | በስታንዳርድ መሠረት የተሰጠ ፈጣን አገልግሎት | | • ለኢትዮጵያዊያን / ትውልድ ኢትዮጵያውያን የፀና ፓስፖርት ወይም የትውልድ ኢትዮጵያዊ መታወቂያ ካርድ<br>• የጎረቤት አገሮችና የአባይ ተፋሰስ አገሮች ዜጎች የፀና የዜግነት ፓስፖርት ወይም ሌላ ህጋዊ ዶክመንት<br>• አንድ የፓስፖርት መጠን ባለቀለም ፎቶግራፍ (በነጭ መደብ) | |

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 8 | በግብር ከፋይነት ለሚመዘገቡ ኢትዮጵያውያንና ትውልድ ኢትዮጵያውያን አገልግሎት መስጠት | 10-20 ደቂቃ | በስታንዳርድ መሠረት የተሰጠ ፈጣን አገልግሎት | | • የፀና ፓስፖርት / የትውልድ ኢትዮጵያዊ መታወቂያ ካርድ ወይም የመኖሪያ ፈቃድ ቅጂ<br>• ለውጭ ዜጎች የፀና የፓስፖርት፣የስራና የመኖሪያ ፈቃድ ቅጂ<br>• አንድ የፓስፖርት መጠን ያለው ባለቀለም ፎቶግራፍ (በነጭ መደብ)<br>• የተሞላ የግል መረጃ<br>• የአገልግሎት ክፍያ መፈጸም፣ | ለኢትዮጵያውያን እና ትውልድኢትዮጵያዊያን **540 SEK**<br>ለውጭ ዜጎች **827 SEK** |
| 9 | ከምንሸፍናቸው አገሮች ጠቅልለው ወደ አገራቸው የሚመለሱ የዲያስፖራ አባላት መገልገያ ዕቃዎች ይዘው እንዲገቡ የድጋፍ አገልግሎት መስጠት | ከ20-30 ደቂቃ | የተሰጠ ፈጣን አገልግሎት | | • የፀና ፓስፖርት / ትውልድ ኢትዮጵያዊ መታወቂያ ካርድ እና የመኖሪያ ፈቃድ ቅጂ<br>• የድጋፍ ጥያቄውን በጽሑፍ ማቅረብ<br>• 5 አመትና ከዚያ በላይ የውጭ አገር ቆይታን የሚገልጽ ማስረጃ<br>• የሚኖሩበትን አገር ለመልቀቅ መዘጋጀታቸውን የሚገልጽ ለመጨረሻ ጊዜ ታክስ ያሳወጁበት፣ቤት የለቀቁበት እና ስራ የለቀቁበት ማስረጃ<br>• ከፍተኛ ትምህርታቸውን ተከታትለው ለሚመለሱ ተማሪዎች ትምህርት ላይ መቆየታቸውን የሚገልጽ የዩኒቨርሲቲ የድጋፍ ደብዳቤና በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር የተረጋገጠ የትምህርት ማስረጃ<br>• ለጡረተኞች የጡረታ መታወቂያ ወይም ማስረጃ<br>• በጉምሩክ ባለስልጣን የዕቃዎች ኮድ መሰረት የተሞላ የመገልገያ ዕቃዎች ዝርዝር | |
| 10 | በኢንቨስትመንት ሂደት ችግር ለሚያጋጥማቸው የዳያስፖራ አባላት አስፈላጊውን ድጋፍ መስጠት | 1 ሰዓት | በስታንዳርድ መሠረት የተሰጠ ፈጣን አገልግሎት | | • የፀና ፓስፖርት / ትውልድ ኢትዮጵያዊ መታወቂያ ካርድ እና የመኖሪያ ፈቃድ ቅጂ<br>• የኢንቨስትመንት ወይም የንግድ ፈቃድ ቅጂ<br>• ያጋጠመውን ችግር የሚገልጽ ማመልከቻ | |

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| **4. በፐብሊክ ዲፕሎማሲ ዘርፍ የሚሰጡ አገልግሎቶች** | | | | | | |
| 1 | ወደ አገራችን የሚገቡ ጋዜጠኞች የሚዲያና የቪዛ ፈቃድ እንዲያገኙ ድጋፍ መስጠት | 15 ቀን | በስታንዳርድ መሠረት የተሰጠ ፈጣን አገልግሎት | | • የፓስፖርት ኮፒ<br>• ከሚሰራበት ተቋም የጉዞውን ዓላማ የሚገልጽ ደብዳቤ<br>• የሚይዛቸው የሚዲያ ዕቃዎች ዝርዝር | ------------ |
| 2 | የኤምባሲውን ድረ-ገጽ እና ሶሻል ሚዲያዎች በመጠቀም ወቅታዊ መረጃዎች ለተጠቃሚዎች ተደራሽ ማድረግ | በየዕለቱ | ጥራቱን የጠበቀ መረጃ | | - | |
| 3 | ከኤምባሲው ጋር ግንኙነት ለፈጠሩ ቲንክ ታንኮች እና የሚዲያ ተቋማት ለሀገር ገጽታ ግንባታ የሚረዱ ወቅታዊ መረጃዎች ማድረስ | በየሁለት ሳምንቱ | የተሰራጨ ወቅታዊ መረጃ | | - | |
| 4 | ከጋዜጠኞችና የሚዲያ ተቋማት ለሚቀርቡ ጥያቄዎች አፋጣኝ ምላሽ መስጠት | ጥያቄው በቀረበ ዕለት | የተሰጠ ወቅታዊ መልስ | | - | |
| 5 | የአፍሪካ ቀንድ ትንተና A Week in the Horn ለተጠቃሚዎች ተደራሽ ማድረግ | በየሳምንቱ | የተሰራጨ ወቅታዊ መረጃ | | - | |
| 6 | የኤምባሲውን "ሀገሬ ቡለቲን " በማዘጋጀት ለተደራሾች ማሰራጨት | በየወሩ | የተሰራጨ ወቅታዊ ጽሁፍ | | - | |
| 7 | የውጭ ሚዲያዎች አገራችንን አስመልከቶ የሚያወጧቸውን ዘገባዎች ተርጉሞ ለተጠቃሚዎች ተደራሽ ማድረግ | በየቀኑ ሞኒተር በማድረግ | የአገራችንን ትክክለኛ ገጽታ የሚያሳይ ዘገባ | | - | |